በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግስት
ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮRef. No
አሶሳ፣
The Benishangul Gumuz Regional State
Bureau of Finance & Economic Development
Assosa.፣

ቁጥር ፓ2/222/05/14
ቀን 18/04/14

በአባሪዉ ለተዘረዘሩት ሁሉ

ባሉበት፤

ጉዳዩ፣የተሽከርካሪ ጥገናን ይመለከታል

የክልሉ ገ/ኢ/ል/ቢሮ የተሽከርካሪ ጥገና ወጥና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲጠገን ለማድረግ እንዲቻል የአሠራር መመሪያዎችን፣ማንዋሎችንና ሰርኩላሮችን እያወጣ ተግባራዊ ሲደረግ እንደነበረ እና በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በኩልም ሁለት ሰርኩላሮች የተላለፉ ሲሆኑ ማለትም ፡-

1. በደ/ቁ 321/ከ-1/ልዩ 008 በቀን 17 /02/2005 ዓ/ም በተላለፈው ሰርኩላር ላይ የመኪና መለዋወጫ በቀጥታ ከካምፓኒዎች እንዲገዛና ጥገናው በመንግስት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲፈጸም፣

2. በደ/ቁ1280 ከ-1/ውሰኔ-002 በቀን 06/04/2005 በተላለፈው ሠረኩላርም በካቢኔ ማዕረግ ለተሾሙ አመራሮች መኪና እስከ 500,000 /አምስት መቶ ሺ/ድረስ ቀጥታ ሜኢንኮ አስገብቶ ማስጠገን እንደሚቻል ሰርኩላሮች የተላለፉ ሲሆኑ፣

3. እነዚህ ከላይ የተገለጹ ሰርኩላሮችም በተሻሻለው የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 27/2012 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 3 ውስጥ ተካቶ ሥራ ላይ እንዲዉሉ ተደርጓል፡፡

ሆኖም አንዳንድ ወረዳዎችና ቢሮዎች ይህንን ወደ ጎን በመተው ወጪ ቆጣቢነቱንና አዋጭነቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተሽከርካሪዎችን በቀጥታ ወደ አስመጪ ድርጅቶች ጋራዥ አስገብተው እያስጠገኑ የመመሪያ ጥሰት እየተፈፀመ ከመሆኑም ባሻገር መንግስትን ለተጭማሪ ወጪ እየዳረጉ የሀብት ብክነት እያስከተሉ ስለሆነ ተሽከርካሪዎች ለጥገና ከመላካቸው በፊት የአገልግሎት ዘመናቸው፣ ለጥገና የሚወጣውን ወጪ እና ከጥገና በኋላ የአገልግሎት ዘመናቸው ከወጣባቸው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑ ታይቶ አዋጭነቱ ተረጋግጦ እንዲጠገን

እ ባክዎ መልሱን ሲጽፉልን የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ፡፡ ☎ 057 775 06 74 75 00 0579
Note :- Please Quote our Ref.No. When Replying. (Fax) 057 775 01 64Assosa, Ethiopia

በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግስት
ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮRef. No
አሶሳ፣
The Benishangul Gumuz Regional State
Bureau of Finance & Economic Development
Assosa,፣

ቁጥር______________

ቀን------------------

ሆኖ ማንኛውም መኪና ጥገና ከመሄዱ በፊት ሊያስወጣ የሚችለው ወጪ አስቀድሞ የተገመተ እና በበጀት የተደገፈ መሆኑ ሳይረጋጥ ለጥገና ሊላኩ አይገባ። ስለሆነም አስገዳጅ በሆነ አግባብ የክልሉ የበላይ አመራሮች፣ የክልሉ ካቢኔ እና በዚህ ደረጃ ለተሾሙ አመራሮች መኪና አዲስ ከሆነ እና የመኪናው የውስጥ ሞተር ስሪት ዉስብስብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞዉ በግል ጋራዦች ሲጠገኑ ለተጨማሪ ብልሽት የሚዳርጉ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ በአስመጭ ካምፓኒዎች አስገብተው እስከ 500,000/አምስት መቶ ሺህ ብር/ ብቻ እንዲያስጠግኑ እየገለፅኩ፤ ሆኖ ከዚህ ከተጠቀሱት ውጭ ያሉት የመኪና ጥገናዎች በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 27/2012 አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ በተደነገገዉ አግባብ የተሸከርካሪዉ መለዋወጫ ዕቃዎች ከተሸርካሪ አቅራቢ ድርጅቶች በመግዛት፤ የጥገና ሥራዉ ሌሎች አቅራቢ ድርጅቶችን በጨረታ በማወዳደር አሸናፊ ከሆነ ድርጅት ጋር ዉል በመግባት ጥገና ማድረግ እንደሚገባ አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ዚያድ አብዱላሂ ዓለሚን
Ziyad Abdulahi Alamin

**ግልባጭ**

- ለቤ/ጉ/ክ/መ/መስተዳደር ም/ቤት
- ለቤ/ጉ/ክ/መ/መስተዳደር ም/ቤት የፋ/በ/ጉ/ቋሚ ኮሚቴ
- ለቤ/ጉ/ክ/ዋና ኦዲት መ/ቤት
- ለቤ/ጉ/ክ/መ/ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን
- አሶሳ፤

ለፋ/ዘ/ም/ቢሮ ኃላፊ
ለፐ/ዘ/ም/ቢሮ ኃላፊ
- ለኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት

በቢሮው፤